# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)


## “ ክቡር ሞቱ ለጻድቅ “

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ምዕመናን ልጆቻቸውን ያለመታከት በቅንነት ያገለገሉት ታላቁ ሐዋርያ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ከዚህ ዓለም ድካም ማለፋቸውን የሰማነው በታላቅ ሃዘን ነው። ምንም እንኳን የጻድቅ ሰው ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ መሆኑን ብንረዳም ብፁዕ አባታችን የትም በየአገሩ ለተበታተኑት ኢትዮጵያውያን አማኞች እንደ አባት መካሪ፣ እንደ መምህር አስተማሪ በመሆን በቅዱስ ቡራኬያቸው ጥንካሬና ጽናትን የሚያድሉ የመንፈስ አባት ነበሩ።

ታላቁ መንፈሳዊ አባት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ በገዳም ሕይወታቸውም ሆነ በጵጵስና ዘመናቸው እጅግ ከፍተኛ ትሩፋቶች መፈጸማቸውን ከዜና መዋዕላቸው መረዳት ይቻላል። ብፁዕነታቸው ለሃይማኖታቸው ቀናኢነት ያሳለፉት ገድል፣ የነበራቸው ጽናትና ቅድስና ምንጊዜም የሚታወስ ነው።

ብፁዕነታቸው ለእናት ሀገራቸውና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላምና የተረጋጋ ሁኔታ እንዲፈጠር በዘወትር ፀሎታቸው የሚማለዱ የአገርና የሕዝብ አለኝታ ነበሩ። በወያኔ ኢህአዴግ መሠሪ ደባ ከሚወዷት አገራቸውና ምዕመናን ልጆቻቸው ተለይተው በስደት ቢኖሩም ዛሬ በሀገር ውስጥ በረሀብ የሚቆሉትን፣ የታረዙትን፣ መጠጊያ ያጡትን፣ በሆነ ባልሆነው እየታፈሱ በየእስር ቤቱ የሚማቀቁትን ወገኖች እግዚአብሔር የምህረት እጁን እንዲዘረጋላቸው የዘወትር ፀሎታቸው ነበር።

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ታላቁን መንፈሳዊ አባት ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስን በማጣታችን የተሰማውን ከፍተኛ ሃዘን እየገለፀ የብፁዕ አባታችንን ነፍስ  በአብርሃም እቅፍ እንዲያኖር እንመኛለን።

የኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ምክር ቤት
የካቲት ፲፩ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ. ም
February 18, 2010


**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Siver Spring , MD 20910**

**P.O.Box 8141**
**Silver Spring, MD 20910**

**P.O.Box 88675**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 301-578-4466** **Fax: 301-449-8363** **Email Address:** **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**